
# ስለ ኢስላም አጭር ማብራሪያ

# التعريف الموجز بالإسلام

ዝግጅት

ترجمة : أبوجنيد



الأمهرية

በሳዑዲ ዓረብያ
የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
በመዲና ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ
የጥናትና የምርምር ማዕከል
የትርጉም ክፍል

www.iu.edu.sa

# ስለ ኢስላም አጭር ማብራሪያ

ዝግጅት

በመዲና ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ
የጥናትና የምርምር ማዕከል

ትርጉም

አቡ ጁነይድ ሳልሕ

التعريف الموجز
بالإسلام باللغة الأمهرية

بسم الله الرحمن الرحيم

# መቅድም

ምስጋና ከባሮቹ የሻውን በችሮ ውና በዕዝነቱ ወደ ኢስላም ለመራው ዕንዲሁም በጥበቡ ኢስላምን ችላ ያለን አጥምሞ በጨለማ ውስጥ ዕንዲዋልል ላደረገው ጌ ለአላህﷻ ነው፡፡

ሰላምና ዕዝነት በተላኩት አበሳሪና አስጠንቃቂ ፣ በርሱ(በአላህ) ፈቃድ ወደ አላህ ተጣሪ ፣ ዕንዲሁም ለአለም ብርሃን ፈንጣቂ በሆኑት የመጨረሻው መልዕክተኛ በሙሐመድﷺ ላይ ይሁን፡፡

አላህﷻ ዕንዲህ ይላል ፦ « ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈፅሞ ከዕርሱ ተቀባይነት የለውም ፣ ዕርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው ፡፡» አል-ዒምራን 85 .

የአለማት ጌ ጥራት ይገባውና ከኢስላም ውጪ ማንኛውም ሀይማኖት ከንቱ ዕንደሆነና ተቀባይነት ዕንደሌለው ፣ ዕርሱን የተቀበለም ሰው የከሰረና የጠፋ መሆኑን አብራርቷል፡፡

ዕንደሚ ወቀው ባለንበት ዘመን አብዛኛው ህዝብ ቀጥተኛውን መንገድ የሳተ አላህንም የካደ ነው ፣ ይህም ማለት የአይሁድ ፣ የክርስትና፣ የቡድሃ፣ የሂንዱና የኮሚኒዝም አማኞች ዕንዲሁም የተቀሩት የባዕድ አምልኮ ተከ ዮች ሁሉ ማለት ነው፡፡

አላህ ﷻ ወደ ኢስላም የመራውና መልካም ዕድል የገጠመው ፣ ዕንዲሁም ዕውነትን ለማብራራት ችሎ የሰጠው ሰው ኢስላምን ሊያደርስላቸው፣ወደርሱም ሊጠራቸው ይገባል:: ይህም በነርሱ ላይ ማስረጃ ዕንዲሆን ምናልባትም ወደ ኢስላም ይገቡ ዘንድ ነው::

አንድ ሰው የመጀመሪያው የዳዕዋ (ሰበካ) ዕርምጃው የሚጣራለትን ዓላማ ማሳወቅ ዕንደመሆኑ ይህ አጭር መፅሐፍ ኢስላምን በማስተዋወቁ ረገድ አጋዥ ይሆናል::አላህ ﷻ ጭፍን ልቦናን የሚከፍት፣የደነቆረ ጆሮን የሚያሰማ፣የ ወረ ዓይንን የሚያበራ ዕንዲያደርገውና ፍሬያማ ዕንዲሆን ዕንመኛለን::

ይህ አጭር መፅሓፍ ለአዳዲስ ሙስሊሞች ስለ ሃይማኖ ቸው አጠር ባለ መልኩ ትክክለኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚረዳ ነው::ይህም በአላህ ፈቃድ ዕስልምናቸው ያማረ ዕንዲሆን በርሱም ላይ ዕንዲፀኑ በኢስላማዊውም ጥሪ በመሳተፍ ኢስላምን በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች ዕንዲያደርሱ አስተዋፅኦ ያደርጋል::የዳዕዋንና የትግልን ባንዲራ ዕንዲያነግቡ ያግዛቸዋል::ፀጋ በአላህ ﷻ ዕጅ ነው::ለፈለገው ይሰጠዋል::

ምስጋና ለዓለማት ጌ ለአላህ ﷻ ነው !!

በመዲና ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ
የጥናትና የምርምር ማዕከል

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

# ኢስላም አጭር ማብ

*ምስጋና ለአለማት ጌ ለአላህ የተገባ ነው:: የአላህ ሰላምና ዕዝነት የመልዕክተኞች መሪ በሆኑት ነብይ በሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን::*

ኢስላም ማለት *«ከአላህ ሌላ በሀቅ የሚመለክ ጌ የለም፣ሙሐመድﷺ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው»* ብሎ በልቦና ማመን፣ በአንደበት *መመ*ስከርና በተግባርም ማረጋገጥ፣በስድስቱ የኢማን *መሰረቶች* ማመንና አምስቱን የኢስላም *መስረቶች መፈፀም ዕንዲሁም* ይህንኑ ስራ ባማረ *መ*ልኩ *መፈጸምን*(ኢህሳንን) ያጠቃልላል::

ኢስላም ፧ አላህ የነብያትና የመልዕተኞች (ሩሱሎች) መደምደሚያ በሆኑት በዓብደላህ ልጅ ሙሐመድﷺ ላይ ያወረደው የመልዕክቶቹ ሁሉ መቋጫ ነው:: አላህ ዘንድም ከኢስላም በቀር ተቀባይነት ያለው ሀይማኖት የለም:: ይህንን ዕውነተኛ ሀይማኖት አላህﷻ ገርና ቀላል፣ አዳጋችም ሆነ አሰቸጋሪ ነገር የሌለበት አድርጎ ል:: አማኞችን ከአቅም በላይ የሆነ ትዕዛዝ አላዘዛቸውም:: የማይችሉትንም ግዴ አላደረገባቸውም:: ኢስላም መሰረቱ የአላህ አንድነት፣ መለያው ዕውነተኝነት፣ ዛቢያው ፍትህ ፣ መነሻው ሀቅና ዕዝነት ነው:: ኢስላም ሰዎችን በመንፈሳዊ ሕይወ ቸውም ሆነ ለዓለማዊ

ኑሯቸው ጠቃሚ ወደ ሆነ ነገር ሁሉ የሚመራ፣ በአንፃሩም ጎጂ ከሆነ ነገር ሁሉ የሚያስጠነቅቅ ላቅ ሀይማኖት ነው።

ኢስላም አላህ ﷻ የሰው ልጆችን ዕምነትና ባህሪ ያስተካከለበት፣ የዱንያንና የአኺራን ህይወት ያሳመረበት፣ የተራራቁ አመለካከቶችንና የተለያዩ ዝንባሌዎችን አንድ በማድረግ ከንቱ ከሆነ ፅልመት አጥርቶ ወደ ዕውነት የመራበት ሀይማኖት ነው። አጠቃላይ ህግጋቱም ሆነ መልዕክቶቹ ፍፁም በሆነ መልኩ ተብራርተዋል። ኢስላም ሀቅን ዕንጂ አልተናገረም! በዕውነትና በፍትህ ዕንጂ አልፈረደም! ትክክለኛ ዕምነትን፣ ቀና የሆነ ተግባርን፣ የላቀ ባህሪን ዕንዲሁም ላቅ ስርዓትን አስተምሯል።

የኢስላም መልዕክት የሚከተሉትን ዓላማዎች ያካት ል:-

1- የመጀመሪያው ዓላማው የሰው ልጆችን ከፈጣሪያቸው ጋር ማስተዋወቅ ሲሆን ያማሩ ስሞቹ ወደር ዕንደሌላቸው ፣ መልካም ባህሪያቱ ምሳሌ ዕንደሌላቸው ፣ በጥበብ የተሞሉ ስራዎቹንም ማንም ዕንደማይጋራው፣ ዕንዲሁም አምልኮ(ዒባዳ) ለርሱ ብቻ ዕንደሚገባ በዚህም ቢ.ጤ ዕንደሌለው ያስተምራል።

2- የሰው ልጆች አላህ በቁርኣንና በሀዲስ የደነገጋቸውን በዱንያም ሆነ በአኺራ ስኬ ማ የሚያደርጋቸውን ትዕዛዛቱን ዕንዲፈጽሙ፣ ከከለከላቸውም ነገሮች ዕነዲቆጠቡ፣ በዚህም አጋር የሌለውን አላህን ብቻ ዕንዲያመልኩ ይጣራል።

3- ከሞት በኋላ የሚኖራቸውን ዕጣ ፈንታ ፣ በቀብር ውስጥ የሚያጋጥማቸውን ሁኔ ፣ በትንሳኤ ቀን ያለውን ክስተትና አላህም ዕንደሚተሳሰባቸው ዕንዲሁም የመልካም ስራ ዋጋ መልካም፣ የክፉ ስራ ምንዳም ክፉ መሆኑንና ዕንደየስራቸውም መጨረሻቸው ወደ ጀነት ወይም ወደ ዕሳት ዕንደሚሆን ያስገነዝባቸዋል።

ከዚህ በመቀጠል ዋና ዋናዎቹን የኢስላም መርሆዎች አጠር ባለ መልኩ ለማብራራት ዕንሞክራለን።

## ነል ኢማን (የዕምነት ማዕዘ

**1-በአላህ ማመን-** በአላህ ማመን የሚከተሉትን ነጥቦች ያካት ል::

1.1- በአላህ ጌትነት ማመን:- አላህ ፈጣሪ ጌ ና የሁሉ ነገር ባለቤት ዕንደሆነ፣ የፍጡራንን ዕንቅስቃሴዎች በሙሉ ዕንደሚያስተናብርና በነርሱም ላይ ሙሉ ስልጣን ዕንዳለው ማመን ነው::

1.2- በአላህ ብቸኛ ተመላኪነት ማመን:- አላህ ዕውነተኛ አምላክ ዕንደሆነና ከርሱ ሌላ የሚመለክ ማንኛውም አካል ከንቱ ዕንደሆነ ማመን ነው::

1.3- በአላህ ስሞችና ባህሪያት ማመን:- በቁርኣንና በሀዲስ በተገለፀው መሰረት አላህ መልካም ሰሞችና የላቁ ምሉዕ የሆኑ ባህሪያት ዕንዳሉት ማመን ነው::

**2-በመላዕክት ማመን-**መላኢኮች ዘውትር አላህን የሚገዙ፣ ለትዕዛዛቱም ተገዢ የሆኑ አላህ የፈጠራቸው የተከበሩ ባሮቹ ናቸው:: አላህ የተለያየ የስራ ድርሻ ሰጥቷቸዋል:: ከነርሱ መካከል ጂብሪል የተባለው የወሕይ (ከአላህ ወደ ነብያት የሚወርድ መልዕክት) ወኪል ሲሆን ከነብያትና ከሩሱሎች አላህ ወደሻው የወሕይን መልዕክት ይዞ ይወርዳል:: ሚካል(ሚካኢል) የተባለው መልዐክ ደግሞ ለዝናብና ለተክሎች የተመደበ ነው:: ኢስራፊል ደግሞ በዓለም ጥፋትና በትንሳኤ ቀን በቀንድ ለመንፋት ተመድቧል::

ዕንዲሁም መለኩልመውት የተባለው መልዐክ በሞት ጊዜ ነፍስን ለማውጣት ተመድቧል።

3-በመፅሐፍት ማመን- አላህ በመልዕክተኞቹ ላይ ቅን መመሪያ፣ ፀጋና ተህድሶን ያዘሉ መፅሐፍትን አውርዷል። ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉትን ዕናውቃለን።

📖 ተውራት- አላህ በነብዩ ሙሳ ﷺ ላይ ያወረደው ሲሆን ለኢስራኤል ልጆች ከተሰጡት ላላቅ መፅሐፍት አንዱ ነው።

📖 ኢንጂል- አላህ በነብዩ ዒሳ ﷺ ላይ ያወረደው መፅሐፍ ነው።

📖 ዘቡር- አላህ ለነብዩ ዳዉድ ﷺ የሰጠው ነው።

📖 ሱሑፍ- ለነብዩ ኢብራሂም ﷺ የተሰጠ ነው።

📖 ላቁ ቁርኣን- አላህ በመጨረሻው ነብይ በሙሐመድ ﷺ ላይ ያወረደው ሲሆን ከርሱ በስተፊት የነበሩ መፅሐፍትን በሙሉ አላህ በርሱ ሽሯል። ቁርኣን ዕስከ ዕለተ-ትንሳኤ በፍጡራን ላይ በአጠቃላይ ማስረጃ ሆኖ ስለሚኖር የጥበቃውን ዋስትና አላህ ወስዷል።

4-በሩሱሎች(በመልዕክተኞች) ማመን- አላህ ወደ ፍጡራን መልዕክተኞችን ልኳል። የመጀመሪያው ኑህ ﷺ ሲሆኑ የመጨረሻው ደግሞ ሙሐመድ ﷺ ናቸው። የመርየም ልጅ ዒሳንና ዑዘይርን ጨምሮ (የአላህ ሰላምና ዕዝነት በነርሱ ላይ ይሁን) ሰው የሆኑ ፍጡራን ናቸው። የአላህን ብቸኛ ጌትነት የሚያጋራቸው ምንም ዓይነት መለኮ ዊ ባሕሪ የላቸውም። አላህ ከባሮቹ መካከል መልዕክት አድራሾች በማድረግ አክብሯቸዋል።አላህም መልዕክቱን በሙሐመድ ﷺ ላይ ባወረደው ዘልዓለማዊ ኪዳን ደምድሟል።ለሰው ዘር በሙሉም ልኳቸዋል። ከርሳቸው በኋላ ነብይ የለም።

5-በመጨረሻው ቀን ማመን- የመጨረሻው ቀን አላህ ፍጥረ ትን በሙሉ የሚሰበስብበት፣ የሰው ልጆችን ላቅ ተድላ ወይም አሳማሚ ቅጣት ባለበት ዓለም ዕንዲኖሩ ከመቃብራቸው ሕያው አድርጎ የሚያስነሳበት ቀን ነው:: በመጨረሻው ቀን ማመን ከሞት በ ላ ባሉ ክስተቶች በሙሉ ማመንን ያካት ል:: ይህም በቀብር ፈተና፣ በውስጡ ባለው ጸጋና ቅጣት ከዚያም በኋላ በሚከሰተው ዕንደ ትንሳኤ፣ መሰብሰብና መመርመር ዕንዲሁም ጀነትና ጀሀነም ውስጥ ባለው ሁሉ ማመንን ያጠቃልላል::

6-በቀደር(በውሳኔ) ማመን- በቀደር ማመን ማለት አላህﷻ ቀድሞ ባወቀውና ጥበቡ በፈረደው መሰረት ክስተቶችን ዕንደወሰነ በዚሁም መሰረት ፍጡራንን ዕንዳስገኘ ማመን ነው:: አላህ ዘንድ ሁሉም ነገር ጥንቱን የ ወቀ ነው:: በተጠበቀው ሰሌዳም የሰፈረ ነው:: አላህ ሁሉንም በፍላጎቱ ፈጥሯል:: በአላህ ፍላጎት፣ ከዋኔና መፍጠር በቀር የሚከሰት ነገር የለም::

❁ ❁ ❁ ❁ ❁

## አርካኑል ኢስላም (የኢስላም ማዕዘናት)

ኢስላም በአምስት መሰረቶች ላይ የተገነባ ነው:: ማንኛውም ሰው ትክክለኛ ሙስሊም ሊሆን የሚችለው በነርሱ አምኖ ተግባራዊ ሲያደርጋቸው ብቻ ነው:: ዕነርሱም :-

**1-** *«ላ ኢላሀ ኢልለላሀ ሙሐመዱን ረሱሉላሀ»* (ከአላህ በቀር አምላክ የለም፡ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው) ብሎ መመስከር ነው:: ይህች የምስክርነት ቃል ወደ ኢስላም መግቢያ ቁልፍ ናት:: ኢስላምም የሚገነባው ዕርሷን መሰረት አድርጎ ነው:: አላህ ዕውነተኛው አምላክ ነው:: ከርሱ በቀር ያሉ አማልክት በሙሉ ከንቱ ናቸው:: «ኢላሀ» ማለት «መዕቡድ» ወይም የሚመለክ ማለት ነው::

በነብዩ ሙሐመድﷺ መልዕክተኝነት ማመን ማለት ደግሞ ነብዩﷺ የተናገሩትን ዕውነት ብሎ መቀበል፣ ያዘዙትን መ ዘዝ፣ ያወገዙትንና የከለከሉትን መከልከል ዕንዲሁም አላህን ዕርሳቸው በደነገጉት መሰረት ብቻ ማምለክ ማለት ነው::

2- ሰላት:- በቀንና በማ  አምስት ጊዜ የሚፈፀሙ አምስት ሰላቶች(ስግደቶች) ናቸው:: አላህ በባሮቹ ላይ ያለውን ሀቅ ዕንዲወጡ፣ ለፀጋዎቹም ምስጋና ዕንዲያደርሱና ከአፀያፊና ከተጠላ ተግባር ከልካይ ዕንዲሆንላቸው ሰላትን ደንግጎላቸዋል:: ሰላት ከዝሙትና ከፀያፍ ተግባር ሁሉ ይጠብቃል:: በአንድ ሙስሊምና በጌ ው መካከል አገናኝ

ስለሆነ ሙስሊም በሰላቱ ውስጥ ጌ ውን ይማፀናል:: በሚስጥርም ወደርሱ ይፀልያል::

እላህም የሃይማኖት ፅድቀት የኢማን ጥንካሬ ዕንዲሁም ቅርብና ሩቅ መልካም ምንዳ ሰላትን ተከትሎ ዕነዲመጣ አድርጓል:: መልካም ምንዳንም ያስገኛል:: ዕንዲሁም ላቅ አካላዊና መንፈሳዊ ዕርካ ን ይሰጣል:: ከዚህም ባሻገር በዱንያም ሆነ በአኺራ ስኬ ማ ያደርጋል::

3- ዘካ:- ዘካ ማለት ግዴ የሆነበት ሰው በየአመቱ ለሚገባቸው ችግረኞችና ለሌሎች ዘካ ዕንዲወስዱ ለተፈቀደላቸው ሰዎች የሚከፍለው ሰደቃ(ምፅዋት) ነው:: የዘካን ኒሷብ(ዘካ ግዴ የሚሆንበት እነስተኛው የገንዘብ መጠን) የደረሰ ገንዘብ በሌለው ሰው ላይ ግዴ አይሆንም:: ግዴ የሚሆነው በባለሀብቶች ላይ ሲሆን ይህም ሀይማኖ ዊ ግዴ ቸውን ዕንዲወጡና ኢስላማዊ ባህሪ በውስጣቸው ዕንዲያብብ ነው:: ዕንደዚሁም ዘካ በአንድ ሙስሊምና በንብረቱ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ ጥፋቶች ይከላከላል:: ከፈፀመው ወንጀልም ያፀዳዋል:: ለችግረኞችና ዕርዳ ለሚሹ ወገኖች ድጋፍ ይሆናል:: ብሎም ለማህበራዊ ችግሮች መፍትሄ ይሆናል:: ከመሆኑም ጋር ይህ ምፅዋት (ዘካት) ለባለሀብቶች እላህ ከሰጣቸው ገንዘብና ንብረት ጋር ሲነፃፀር በጣም ጥቂት ነው::

4- ፆም:- ፆም ማለት በየአመቱ ዕንደ ጨረቃ አቆጣጠር በዘጠነኛው ወር የተከበረውን ወርሃ ረመዳን መፆም ነው:: በረመዳን በየቀኑ ጎህ ከቀደደበት ጊዜ ጀምሮ ጀምበር ዕስክትጠልቅ ባለው ጊዜ በኢስላም ከተወሰኑ አንዳንድ መሰረ ዊ ፍላጎቶች:- ከምግብ፣ መጠጥና ስጋዊ ተራክቦ በመቆጠብ የአለም ሙስሊሞች በሙሉ በአንድ

አይነት ሁኔ ይፆሙ ል። አላህም በዚህ መልካም ተግባራቸው ከችሮ ው በጎ በመዋልና ኢማናቸውን በመሙላት ይክሳቸዋል። ወንጀላቸውን ይምርላቸዋል።ዕርሱ ዘንድ ያላቸውን ደረጃ ከፍ ያደርግላቸዋል። ዕንዲሁም አላህ ለፆመኞች ካዘጋጀው የዱንያና የአኺራ መልካም ነገር ሁሉ ይቸርላቸዋል።

5- ሐጅ፡- ሐጅ ማለት ወደ ተከበረው የአላህ ቤት(ካዕባ) ለየት ያለ ዒባዳ(አምልኮ) ለመፈፀም በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚደረግ ጉዞ ነው። ሐጅ በኢስላም ላቅ ቦ ያለው ዒባዳ ነው። አላህ አቅም ባለው ሰው ላይ በሕይወቱ አንድ ጊዜ ግዴ አድርጎ ል። ለሐጅ ስነስርዓት ሙስሊሞች ከመላው ዓለም በምድር ላይ ተመራጭና ቅዱስ በሆነው ስፍራ ይሰባሰባሉ። አንድ ዓይነት ልብስ በመልበስ አንዱን አምላካቸውን ይገዛሉ። በመሪና በተመሪዎች ፣ በሀብ ምና በድሃ፣ በነጭና በጥቁር መካከል ልዩነት የለም። በጊዜና በቦ የተወሰኑ የሐጅ ስራዎችን በአንድነት ያከናውናሉ።ከዋና ዋናዎቹ የሐጅ ተግባራት መካከል በዓረፋ መቆም፣ በተከበረው ካዕባ ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ፣ ሰፋና መርዋ በተባሉት ተራራዎች መካከል መሮጥ ይገኙ ል። ሐጅ ለመቁጠርና ለመዘርዘር የሚያዳግቱ ዕጅግ ብዙ ሀይማኖ ዊና ማሕበራዊ ጥቅሞች አሉት።

❁ ❁ ❁ ❁ ❁

## አል-ኢህሳን

ኢህሳን ማለት በልቦናና በተግባር አላህን ዕንደም የው አድርገህ ማምለክ ነው:: አንተ ባ የው ዕርሱ ያይሃልና! ይህንን በልቦና በማሳደር በነብዩ ﷺ ሱና መሰረት ዒባዳን መከወን ፈለጋቸውንም አለመፃረር ኢህሳን ነው::

۞ ۞ ۞ ۞ ۞

ከዚህ በላይ ስለኢስላም፣ ኢማንና ኢህሳን የሰፈረውን አጠር ያለ ማብራሪያ «ኢስላም» የሚለው መጠሪያ ያካትተዋል::

ዕንደሚ ወቀው ኢስላም የግለሰቦችንም ሆነ የኢስላምዊ ማህበረሰቦችን ሕይወት በዱንያም ሆነ በአኺራ ለስኬት በሚያበቃቸው መልኩ ስርዓት አስይዟል:: ለምሳሌ:- ትዳርን ፈቀደ፤ አበረ ም:: በአንፃሩም ዝሙትንና ግብረ-ሰዶማዊነትን ዕንዲሁም መሰል ፀያፍ ተግባራትን ከለከለ:: ዝምድናን መቀጠልን፣ ለድሆችና ለችግረኞት ማዘንንና መንከባከብን ግዴ አደረገ:: መልካም ፀባይን ሁሉ አስተማረ:: ከመጥፎ ፀባይም ሁሉ በመከልከል አስጠነቀቀ:: ለተከ ዮቹም ከንግድ፣ ከኪራይና ከመሳሰሉት የገቢ ምንጮች የሚገኝን ጥቅም ፈቀደ:: ወለድንና ክልክል የሆኑ ማጭበርበርና ማ ለል ያለባቸውን የንግድ ዘርፎች በሙሉ ዕርም አድርጓል::

ሰዎች ለህግጋቱ ከመገዛትና የሌሎችን መብት ከመጠበቅ አኳያ ዕንደሚለያዩ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዕንደ «ሪዳህ»(ኢስላምን ክዶ መውጣት) ፣ ዝሙት ፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣትና በመሳሰሉት የአላህን ሕግጋት በመጣስ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ከበድ ያለ ቅጣት ደንግጓል። ዕንዲሁም በሰዎች ደም፣ ንብረትና ክብር ላይ በሚፈፀሙ ዕንደ ግድያ፣ ስርቆት፣ ስም ማጥፋት፣ ድብደባና የሰዎችን ንብረት ያለአግባብ መውሰድ በመሳሰሉ ወንጀሎች ላይ ገሳጭ ቅጣቶችን ደንግጓል። ቅጣቶቹም ከወንጀሉ ክብደትና ቅለት ጋር ተመጣጣኝነት ያለው ሲሆን በደልም ሆነ ቸልተኝነት የለበትም።

ዕንደዚሁም ኢስላም በገዢና በተገዢ መካከል ያለውን ግንኙነት በመወሰን አስተዳደርን ስርዓት አስይዟል። ተገዢው ሕዝብ ወንጀል ነክ ባልሆነ ነገር በሙሉ ለገዢው መደብ ዛዥ ዕንዲሆን ግዴ አድርጓል። በግለሰቦችና ባጠቃላይ ማሕበረሰቡ ላይ በሚያስከትለው መዘዝ ሳቢያ አመፅን ከልክሏል።

❁ ❁ ❁ ❁ ❁

በመጨረሻም ይህችን አጠር ያለች መልዕክት በዚህ ማጠቃለያ ሀሳብ ዕነቋጫለን።

✿ ኢስላም በሰው ልጆችና በጌ ቸው፣ በግለሰቦችና በሚኖሩበት ማህበረሰብ መካከል በሁሉም መስክ ትክክለኛና መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ያስችላል። መልካም ባህሪንና ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነትን ለተከ ዮቹ አስተምሯል። በአንጻሩም መጥፎ ከሆነ ባህሪና ሻካራ ከሆነ ግንኙነት ተከ ዮቹን አስጠንቅቋል። ይህም የኢስላምን ምሉዕነትና በሁሉም ጎኑ ለሰው ልጆች የሚበጅ ሰንደሆነ የሚያሳይ ነው።

*ምስጋና ለዓለማት ጌ ለአላህ የተገባ ነው !*

المملكة العربية السعودية
وزارة التعليم العالي
الجامعة الإسلاميّة بالمدينة المنورة
عمادة البحث العلمي
قسم الترجمة

www.iu.edu.sa

# التعريف الموجز بالإسلام

باللغة الأمهرية

المترجم: أبو جنيد صالح